# ገና አልተዋወቅንም!!

ከዘነበ በቀለ

ያገር አፈር ይቅመስ፣ ብለው የሚሉት ቧልት፣
ከየት የመጣ ነው?! ይኸን መሳይ ቅዠት!
ቆይቶ የለም ወይ?! የሀገሩን አፈር፣ ሀይሉ ከቀመሰ፣
ለጋምቤላው ብሎ፣ ለአፋሩ ብሎ፣ ለአማራው ብሎ፣
ለኦሮሞው ብሎ፣ እንዲያው በጠቅላላው ለኢትዮጵያ ሀገሩ፣
ያልተናገረበት የትኛው ዘመን ነው?
የትኛው ዘመን ነው?! ተይዞ በፍርሃት
ሀይሉ ደሃ ከድቶ?! ፀጥ ለጥ ያለበት?!
መቼ ነው ገሞራው?! የወያኔን ደባ ያላጋለጠበት?!
ጭራቅ ብሎ ስሎ፣ ያላወገዘበት?!

የትኛው ዘመን ነው?! ወገኔን አትንኩ ብሎ ያላለበት?!
ላገዛዝ አልመች፣ ብሎ ያላመፀበት?
ኖሯል ታዲያ! ሀይሉ በነዚህ ዘመኑ!
ቀርቶለት ነበረ፣ በየሶስት ወሩ፣ በፖሊስ በአለቃ ታስሮ መመርመሩ?

የትኛው ዘመን ነው፣ አፈር ያልቀመሰበት?
የትኛው ዘመን ነው፣ ሞቶ ያልተነሳበት።
ከትውልድ ለይቶ፣ ለማኖር ደብቆ?
ስራዎቹን ሰርቆ፣ ለመቅበር አርቆ፣
ማሰቡ ማለሙ፣ ተጠቦ ተጨንቆ፣
ሀይሉ አገር ካልገባ፣ ዕቅ እንቅ መባሉ!
ውክልና ለማግኘት፣ እንዲያ መሽከርከሩ!
እውን ወዳጅነት ነው - በማሰብ ለሃይሉ?

ሀይሉማ! ገሞራው፣ ከደሀው ጋር ደሃ - ሆኖ ያልተገኘበት፣
አንደበት ላጣው ህዝብ አንደበቱ ሆኖ ያልተናገረበት፣
ምንም ዘመን የለም፣ ህዝቡ ሲጨፈጨፍ፣ ወጣቱ ሲታረድ ተቀምጦ ያየበት፣
እናም ሀይሉ ኖሮ! ኖሮ! ኖሮ ሞተ - ከመባሉ፣
ሲሞት ሲሞት ኖሮ፣ ሞተ ለትንሳኤ – ይሻላል ብሂሉ!
መጥፋት ብሎ መኖር እንዳለው እራሱ፣
በየመጣጥፉ በብዕር ድግሱ።

ስለዚህ ጎበዝ <u>ሳታመሀኝ ብላኝ</u> ብሏል ከያኒው፣
አመካኝቶ መብላት ስለሰለቸው።
ንግድ የምትነግዱ፣ ባለኮንዶምኒየሞች፣
የልማት ህልመኞች፣ አልሙ በራሳችሁ፣
የምን ጠጋ ጠጋ፣ ሀይሉን መሻታችሁ?!

ከብት ባልዋለበት፣ ኩበት ለምትለቅሙ፣
ምንም ችግር የለም፣ እርስ በርስ ነውና እርስ በርስ ተግማሙ።
ግና! ለናንተ ሊዝ! በተሸጠ መሬት አስከሬኑ እንዲያርፍ ምክንያት የሆናችሁ፣
አትጠራጠሩ! አይቀርም የጃችሁ!